VDH VIRGINIA DEPARTMENT OF HEALTH

# ምን ክትባት ያስፈልግዎታል?

## በ Mpox ስጋት ውስጥ ላሉ እና/ወይም ከኤችአይቪ ጋር ለሚኖሩ ሰዎች የሚመከሩ ክትባቶች




| ክትባት | ስለ ክትባቱ | ማን ሊወስደው እንደሚችል | ለምን እንደሚወስደው | መቼ እንደሚወስደው | የት እንደሚወስደው |
|---|---|---|---|---|---|
| **የኢንፍሉዌንዛ ክትባት** | ከተለመዱ የኢንፍሉዌንዛ ቫይረሶች የሚከላከል ክትባት። | ዕድሜያቸው 6 ወር ወይም ከዚያ በላይ የሆኑ ሰዎች በሙሉ።<br>አንድአንድ ልጆች ብዙ መጠን ሊያስፈልጋቸው ይችላል። | ከበሽታ፣ ሀኪም ቤት መተኛት፣ እና ሞት ሊከላከል ይችላል።<br>በኢንፍሉዌንዛ ለተያዙ ሰዎች፣ የበሽታውን ክብደት ሊቀንስ ይችላል። | በየ አመቱ። የኢንፍሉዌንዛ ክትባትን ለማግኘት ሴፕቴምበር እና ኦክቶበር ምርጥ ወራት ናቸው። | የጤና መምሪያዎች፣ ፋርማሲዎች እና የህክምና ቢሮዎች።<br>በታውን በ vaccinate.virginia.gov ያግኙ |
| **የCOVID-19 ክትባት** | ከኮቪድ-19 ተለዋጮች ለመከላከል በጣም የተለመደ ነው ተብሎ የሚጠበቀው ክትባት። | • ዕድሜያቸው 6 ወር ወይም ከዚያ በላይ የሆኑ ሰዎች በሙሉ።<br>• አንድአንድ ሰዎች (ልጆች፣ የደከመ የመከላከል ስርአቶች ያላቸው፣ እድሜአቸው የገፋ ሰዎች) ብዙ መጠን እንዲያገኙ ይመከር ይሆናል። | ከከፋ በሽታ፣ ሀኪም ቤት መተኛት፣ እና ሞት መከላከል ይችላል።<br>እንዲሁም የረጅም-ጊዜ በኮቪድ የመያዝ ስጋትን ሊቀንስ ይችላል። | የዘመነው የኮቪድ-19 ክትባት በሚገኝበት ጊዜ (አብዛኛውን ጊዜ በመኸር ወቅት)።<br>በቅርቡ የኮቪድ-19 ክትባት ወስደው ከነረ፣ ምርቀዛን-መሰረት ያደረገ የመከላከል አቅም አልዎት እና ከምርቀዛዎ በኋላ ከመከተብዎ በፊት ሶስት ወራት መቆየትን ግምት ውስጥ መክተት ይችላሉ። | የጤና መምሪያዎች፣ ፋርማሲዎች እና የህክምና ቢሮዎች።<br>በታውን በ vaccinate.virginia.gov ያግኙ |
| **የMPOX ክትባት** | Mpoxን ለመከላከል ሁለት-መጠን ክትባት። | • Mpox ካለበት ሰው ጋር የቅርብ ንክኪ የነበራቸው ወይም በmpox የመያዝ ዕድላቸው ከፍተኛ የሆኑ ሰዎች።<br>• በmpox ለመያዝ ስጋት ላይ ያሉ ሰዎች።<br>*ከ mpox ያገገሙ ሰዎች ክትባቱን አያስፈልጋቸውም።* | ከባድ ሕመምን፣ ሆስፒታል መተኛትን እና በmpox ሞትን ይከላከላል።<br>በኢንፍሉዌንዛ ለተያዙ ሰዎች፣ የበሽታውን ክብደት ሊቀንስ ይችላል። | ብቁ ከሆኑ ወዲያውኑ። ለተሻለ ከለላ ሁለቱንም መጠኖች ይውሰዱ።<br>የመጀመሪያ መጠን ከወሰዱ ትንሽ ጊዜ ቆየት ካሉ ፣ ሁለተኛውን ለማግኘት መቼም ቢሆን አልዘገዩም። | አብዛኛዎቹ የጤና መምሪያዎች እና አንዳንድ የህክምና ቢሮዎች።<br>በታውን በ mpoxvaccine.cdc.gov |
| **MENINGOCOCCAL ክትባት** | የማጅራት ገትር በሽታን ለመከላከል የሚረዱ ሁለት አይነት ክትባቶች።<br>እያንዳንዱ የክትባት አይነት ሁለት መጠን ነው። የተወሰነ የስጋት መንስኤዎች ያላቸው አንዳንድ ሰዎች ተጨማሪ ሊያስፈልጋቸው ይችላል። | እንደ ኤችአይቪ ያሉ አንዳንድ የጤና እክሎች ያለባቸው ሁሉም ልጆች፣ ታዳጊዎች እና ሰዎች። | ማጅራት ገትርን ሊያስከትል የሚችለውን የማጅራት ገትር (meningococcal) በሽታን ለመከላከል ይረዳል። | ብቁ ከሆኑ እና የማጅራት ገትር ክትባት ካልተቀበሉ ወዲያውኑ። ለተሻለ ከለላ ሁለቱንም መጠኖች ይውሰዱ። | አብዛኛዎቹ የጤና መምሪያዎች፣ ፋርማሲዎች እና የህክምና ቢሮዎች። |
| **ሌሎች ክትባቶች** | እንደ የመተንፈሻ ሲሳይሺያል ቫይረስ (RSV) ኢንፌክሽን ወይም የሳንባ ምች በሽታ ላሉ በሽታዎች፣ በእድሜዎ፣ በጤና ሁኔታዎ ወይም በሌሎች ምክንያቶች መሰረት ሌሎች ክትባቶች ሊፈልጉ ይችላሉ። ምን አይነት ክትባቶች ለእርስዎ ተገቢ እንደሆኑ ከጤና እንክብካቤ አቅራቢዎ ጋር ይነጋገሩ። | | | | |

**ለበለጠ መረጃ**

**ኢንፍሉዌንዛ እና COVID-19፦ https://www.vdh.virginia.gov/epidemiology/respiratory-diseases-in-virginia/**
**Mpox፦ vdh.virginia.gov/monkeypox/vaccination**
**Meningococcal፦ vdh.virginia.gov/surveillance-and-investigation/meningococcal-disease-outbreak-response**

በብዙ አጋጣሚዎች፣ እነዚህ ክትባቶች በተመሳሳይ ጊዜ ሊሰጡ ይችላሉ። ሆኖም፣ ሁለቱንም mpox እና COVID-19 ክትባቶችን እንዲወስዱ የሚመከሩ ጎረምሶች ወይም ትልቅ ወንዶች በእነዚህ ክትባቶች መካከል አራት ሳምንታት መጠበቅን ግምት ውስጥ ሊከቱ ይገባል። ስለማንኛውም ክትባት ጥያቄዎች ካሉዎት፣ ከጤና እንክብካቤ አቅራቢው ወይም ከፋርማሲስቱ ጋር ይነጋገሩ። የጤና እንክብካቤ አቅራቢ ከሌለዎት፣ የአካባቢዎን የጤና መምሪያ በ **vdh.virginia.gov/health-department-locator** ላይ ያግኙ እና ያነጋገሩት።

*ለመጨረሻ ጊዜ የተዘመነው በ 10/2024*